# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ምዕመናን ዓለም አቀፍ ማኅበር

## WORLD ASSOCIATION OF PARISHIONERS OF E.O.T. CHURCH

ቁጥር፡ ዕሰ 4/225/05

ቀን፡ኅዳር 23, 2005 ዓ.ም

"የትዕግሥት እና የመጽናናት አምላክ እግዚአብሔር እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ፈቃድ
እርስ በእርሳችን አንድ ሐሣብ መሆንን ይስጠን። ሁላችን አንድ ሆነን በአንድ አፍ በጌታችን
በኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሄርን እናመሰግነው ዘንድ።" ሮሜ 15:5፣

### ግልጽ ማመልከቻ

ለብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ፤
ለብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ፤ እና
ለብፁዕ አቡነ ገሪማ

ከኢትዮጵያ

ለብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ
ለብፁዕ አቡነ ኤልያስ፤ እና
ለብፁዕ አቡነ ጐርጐርዮስ

ከአሜሪካ እና ከአውሮጳ

**ብፁዓን አባቶቻችን ሆይ!**

ከሁሉ በማስቀደም፣ ተደራጅቶ ሕጋዊ ሰውነት ከተቀዳጀ አሥር ዓመታትን ያስቆጠረው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስትያን ምዕመናን ዓለም አቀፍ ማኅበራችን፣ ብፁዓን አባቶቻችን በእርቀ ሰላም ድርድር አማካይነት ሐዋርያዊት፣ ጥንታዊት እና ታሪካዊት የሆነችዉን የቅድስት ቤተክርስቲያናችንን አንድነት ለማደስ የምታካሂዱት ጉባዔ ተፈላጊውን ውጤት ያስገኝልን ዘንድ ቸሩ ፈጣሪያችንን እንለምናለን።

በመቀጠልም፣ በፓትርያርክ ሲመት ምክንያት በቤተክርስቲያናችን ውስጥ የተከሰተው የአስተዳደር ክፍፍል በሀገር ውስጥ እና ከሀገር ውጪ የሚገኙትን ብፁዓን አባቶቻችንን ከማለያየት አልፎ እስከማወጋገዝ መድረሱ፤ የቤተክርስቲያናችን ሥረዓታት እና ሕግጋት እየተጣሱ ታሪካዊ አንድነቷ ሊፈርስ በሚችልበት አደገኛ ጐዳና ማዝገም መጀመሯን ጠቋሚ ስለሆነ፣ ውግዘቱ ከቤተክርስቲያናችን ችግሮች ሁሉ ቅድሚያ ትኩረት ተሰጥቶት እንዲሻርልን እና ጐራ ሳንለይ በየአካባቢያችን በሚገኙት ብፁዓን አባቶች መባረክ እና መመራት የምንችልባት ዕለት እንድትብትልን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስን እና ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስን በመለመን ማኅበራችን ጽፎ የነበረውን ደብዳቤ በታላቅ ትህትና ማስታወስ እንሻለን።

አያይዘንም፣ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትሪያርክ ዘኢትዮጵያ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት በፈጣሪያችን ተጠርተው ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ በኋላ፣ መስከረም 27 ቀን 2005 ዓ.ም. በቁጥር ዕሰ2/212/05 አድራሻውን ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ፤ ለብፁዕ አቡነ ናትናኤል አቃቤ መንበረ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ እና የአርሲ ሀገረ ስብከት ሊቀጳጳስ፣ እንዲሁም ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ካህናትና ምዕመናን በሙሉ በጻፍነው ግልጽ ደብዳቤ ደግሞ፣ እርቀ ሰላምን አስመልክቶ የተገለጡልንን ፍሬ ነገሮች እና ለመፍትሔ ይበጃሉ ያልናቸውን ሐሣቦች ዘርዝረን ማቅረባችን እንዳይዘነጋብን በታላቅ አክብሮት እንጠይቃለን።

እነዚህ እና ሌሎች ጥረቶቻችን እንደተጠበቁ ሆነው፣ በሀገር ውስጥ እና ከሀገራችን ውጪ የምትገኙት አባቶቻችን የቤተክርስቲያኗን የሰላም እና የአንድነት ችግር በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ለመፍታት ቆርጣችሁ መነሳታችሁ ያበረታታንን ያህል፣ በሁሉቱም ጐራዎች ተካሂደው የነበሩት የቅዱሳን ሲኖዶሶች ስብሰባዎች ከተጠናቀቁ በኋላ የተስተጋቡት መግለጫዎች የሐሣብ ልዩነቶችን በማንፀባረቃቸው ምክንያት ደግሞ እጅግ ተደናግጠን የነበረ መሆኑን መሸሸግ አንችልም።

4002 Blacksmith Drive, Garland, TX 75044 - www.eotcipc.org
miimenan@yahoo.com; (214)703 9022

ይሁን እንጂ፣ በአዲስ አበባም ሆነ በኮሎምበስ-ኦሃዮ የተካሄዱት የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባዎች የዕርቀ ሰላሙ ድርድር እንዲቀጥል ያሳለፏቸው ውሳኔዎች ተከብረው፣ ሁለቱንም ጐራዎች የምትወክሉት ብፁዓን አባቶቻችን በሦሥተኛው ዙር የሰላምና አንድነት ጉባኤ ላይ ለመገኘት ወደ ዳላስ-ቴክሳስ ማምራታችሁን ስለተረዳን፣ ተስፋችን መለምለሙን ሳንገልጽ አናልፍም።

የእርቀ ሰላም ድርድሩን የምታካሂዱት ብፁዓን አባቶቻችን ከኛ ይልቅ ለቤተክርስቲያናችን ሰላም እና አንድነት አሳቢ መሆናችሁን እናውቃለን። ከሃያ ዓመታት በፊት በተፈጸመው ሲመተ - ፓትርያርክ ሳቢያ ተጀምሮ እየከረረ የሄደው ክፍፍል ከእንግዲህ ቢቀጥል፤ ጠንቁ ሥር እየሰደደ እማይታረቅ ቅራኔ ውስጥ ሊያስገባ መቻሉንም ከእኛ ይበልጥ እንደምትገነዘቡት እናምናለን። ልዑል እግዚአብሔር ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያናችንን ለመታደግ ከማናቸውም ጊዜ ይልቅ ለመፍትሔ ያመቸ ሁኔታ እንደፈጠረልን የማይረዳ ይኖራል ብለንም አናስብም።

የቅራኔ አፈታት ሕግ ወደ ችግሩ ሥረ-መሠረት ገብቶ የወል ግንዛቤ መጨበጥን ቢጠይቅም፣ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የተፈጸሙ ክስተቶችን መርምሮ መረዳት የሚጠይቀው ጥረት ረዥም ጊዜ ሊፈጅ ስለሚችል፣ ውጤታማ የሆነ ድርድር ለማካሄድ ሲተለም አንዳንድ ጉዳዮችን ለታሪክ ፍርድ ትቶ ከማያስማሙ ይልቅ በሚያግባቡ ሐሣቦች ላይ ማተኮሩ ይበልጥ ጠቃሚ ይሆናል። ዋናው መሠረታዊ ችግር፣ በአንድ የታሪክ ወቅት ቤተ ክርስትያናችን ሁለት ፓትርያርኮችን ይዛ ለመንቀሳቀስ በመገደዷ ሳቢያ የተፈጠረው ሁኔታ መሆኑ ስለሚታወቅ፣ በዚሁ የታሪክ ወቅት ብፁዕ ወቀዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ወርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሆነው እንደዘለቁት ሁሉ፤ ብፁዕ ውቅዱስ አቡነ ጳውሎስም በመንበረ ተክለሃይማኖት የተቀመጡ ፓትርያርክ ወርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ እንድነበሩ ተማምኖ መስማማት የግድ ይሆናል።

በዚህ መሠረትም፤ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ በሃያው የፐትርክናቸው ዓመታት ውስጥ በኢትዮጳያ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃም አመራር የሰጡና ታላላቅ ተግባራትን ያከናወኑ አባት መሆናቸው በቤተክርስቲያናችን ታሪክ ውስጥ ጉልህ ምዕራፍ እንደሚኖረው አያጠያይቅም። በአንጻሩ ደግሞ፤ ከአቅማቸው በላይ በሆነ ምክንያት መንበራቸውን ተነጥቀው ለስደት የተዳረጉት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስም ፐትርክናቸውን አሳልፈው ካለመስጠታቸው ባሻገር ከስደተኛ ብፁዓን አባቶች ጋር ቅዱስ ሲኖዶስ እይመሩ ስለዘለቁ፣ ፓትርያርክ አይደሉም ማለት እሩቅ አያስኬድም።

ከሁለቱም ጐራዎች ተወክላችሁ ይህ በአንድ የታሪክ ወቅት የተፈጸመ ዕውነታ የፈጠረውን ችግር ለመፍታት ሐሣብ የምትለዋወጡት ብፁዓን አባቶቻችን ባካበታችሁት የመንፈሳዊ ህይወት ተመክሮ ላይ ተመሥርታችሁ የቤተክርስትያኗን ደህንነት በሚመለከት "አሸናፊ እና ተሸናፊ" ወገን ሊኖር አለመቻሉን ከማንም የበለጠ ስለምታጤኑት እና ድርድራችሁንም "ሰጥቶ በመቀበል" ቅንነት ስለምታከናውኑት፣ መፍትሔው ከጭብጣችሁ ውጪ ይሆናል ብለን አንገምትም።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ዓለም- አቀፍ ማኅበር ቀደም ብለን በጠቀስነው ግልጽ ደብዳቤው ውግዘቱ ቢነሳ፤ ለአዲሱ ፓትርያርክ ምርጫ ባይቸኮል፤ አቡነ መርቆሬዎስ ወደ መንበረ ተክለሃይማኖት ቢመለሱ፤ የቤተ ክረስቲያኗ አስተዳደር በእንደራሴ ቢመራ፤ የኢፌዴሪ መንግሥት የሚጠየቀውን ትብብር ባይነፍግ እና ካህናት እና ምዕመናን በፀሎት ቢተጉ የሚል ዝርዝር ሐሣብ ለመጠቆም የበቃው ከፍ ብለን ባወሳናቸው ግንዛቤዎች ላይ ተመርኩዞ ነበር።

የዛሬውን ግልጽ ማመልከቻችንን መቋጨት የምንሻው ለእርቅና ሰላም ድርድሩ በተሰበሰባችሁት ብፁዓን አባቶቻችን ትጋትና ጥረት ለቤተክርስትያናችን ሰላም እና አንድነት መሠረት ከተጣለ በኋላ፣ የእህት ቤተክርስቲያኖችን ተመክሮ በመፈተሽ ጭምር፣ በተለያዩ የዓለም አካባቢዎች የምንገኝ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ምዕመናን በአንድ ቅዱስ ሲኖዶስ፣ በአንድ ፓትርያርክ እና በአንድ እረኛ የምንመራ አንድ መንጋ መሆን እንችል ዘንድ ወጥነት ያለው ሰንሰለታዊ መዋቅር በአስቸኳይ ተጠንቶ እንዲተገበርልን ልመናችንን በማቅረብ ነው።

ወስብሃት ለእግዚአብሔር

ይሥሐቅ ከፍሌ
የቦርዱ ሰብሳቢ



4002 Blacksmith Drive, Garland, TX 75044 - www.eotcipc.org
miimenan@yahoo.com; (214)703 9022